

## ፨47-2፨

# ጠቃሚ ምክር

## “ነቀፋን ታግሶ ማለፍ አቃተኝ” ለሚሉ

(ካለፈው የሚቀጥለው)

### 4ኛ. ለነቃፊዎች መልስ ለመስጠት አንቸኩል

ፓናማ ካናልን የገነባ መሃንዲስ ኮሎኔል ጆርጅ ጎሳልስ (George Washington Goethals) ሊሠራ በተነሳው ትልቅ ቦይ (ካናል) ቁጥራቸው ብዙ የሆኑ ሁለ ዝቦች ያለማቋረጥ ይነቅፉት ነበር። ነቃፊዎቹ “ይሄ ቦይ ፈጽሞ ሊገነባ አይችልም” ይሉ ነበር። እርሱ ግን ምንም ዓይነት መልስ ሳይሰጥ በሥራው ላይ ቀንና ሰዓት ይተጋ ነበር። ነቀፋ የሚፈራው ረዳቱ ከየአቅጣጫው የሚወረወረውን ነቀፋ ሰምቶ “ለሚነቅፉህ ሰዎች መልስ የማትሰጠው ለምንድነው ሲል ጠየቀው። “በወቅቱ (በጊዜው) መልስ እሰጣለሁ አለው። “እንዴት?” ሲል መልሶ ጠየቀው። ያም ታላቅ መሃንዲስ ፈገግ ብሎ “ተሠርቶ የሚያልቅ ቦይ ራሱ መልስ ይሆናል” አለው። ግሩም አባባል ነው።
በየቦታው የሚነደውን የነቀፋ እሳት እየዞሩ ለማጥፋት መሞከር የሚሮጥ መንገድ አይደለም። በመኖር፣ በመቆየት፣ አንዳንድ ሁኔታዎችን “ጊዜ ራሱ ይገልጸዋል” በማለት ትቶ ማለፉ ይመረጣል። ነቀፌታው ምንም ዓይነት ቢሆን ግንባራችን ሳይታጠፍና ሳንርበተበት የምንሠራውን ሥራ ጥሩ አድርገን እየሠራን ወደፊት እንቀጥል። እኛ ለማስተባበል ሳንሞክር የሥራችን ፍሬ ምስክር ሆኖ የነቃፊዎቻችንን አፍ ማዘጋት ስለሚችል አቋማችንን ለማስረዳት ጊዜያችንን አናጥፋ። ኢዮብ ወዳጆቹ እየከሰሱ ነፍሱን ሲያስጨንቁት ከመለሰላቸው መልስ አንዱ “እግዚአብሔር የማደርገውን ሁሉ ያያል፤ እርምጃዬን ሁሉ ይመለከታል። ሐሰት ተናግሬ እንደሆነ ሰውንም አታልዬ እንደሆነ እግዚአብሔር በትክክለኛ ሚዛን ይመዝነኝ። እውነተኛነቴንም ይወቅ” አለ (ኢዮብ 3፥13፥4-6)።

ይህን ታሪክ “እግዚአብሔር በቀባው ላይ እጅህን አታንሳ፤ አለበለዚያ በቆራሕና በተከታዮቹ ላይ የደረሰው ይደርስብሃል” በማለት አንዳንድ የቤተክርስትያን መሪዎች ያለአግባብ ሲጠቀሙበት ስናይ ቅር ይለናል። ይሄ አነጋገር ትክክለኛ መንፈስ ኖሮአቸው በሕብረታቸው ውስጥ የሚያዩትን ጤናማ ያልሆነውን ነገር ገልጸው የሚናገሩትን አፍ ይዘጋል። ቅሬታን በጥሩ መንፈስ ተነጋግሮ ማስወገድ ዕድገትን ይሰጣል። በጥሩ መንፈስ የቀረበ ቅሬታ፣ በተንኮልና ሹመት በመፈለግ ከሚሰነዘር ነቀፌታ ፍጹም የተለየ መሆኑን አንርሳ።

በቤተ ክርስትያን፣ በመሥሪያ ቤትና በተለያዩ መንፈሳዊም ሆነ ዓለማዊ ድርጅቶች አንዱ ሌላውን መንቀፍ የተለመደ ነው። ነቃፊዎች የሚነቅፉበት የተለያየ ምክንያት አላቸው። ከምክንያታቸው አንዱ የሚነቅፉት ሰው የያዘውን ሹመት ወይንም አገልግሎት በመፈለጋቸው ሊሆን ይችላል። ከ25 ዓመት በፊት አንድ ወንድም በወቅቱ የቤተ ክርስትያን ሽማግሌዎች በሆኑት ላይ ግልጽ ነቀፋ ያሰማ ነበር። ነቀፋውም “እዚህ ቤተ ክርስትያን ጥልቀት ያለውን ትምህርት መስጠት የሚችል የለም” የሚል ነበር። ችሎታችንን ወደ ኋላ መለስ ብዬ ስመዝነው እውነትም በቂ ልምምድ የጎደለን አስተማሪዎች ነበርን፤ ግን በወቅቱ ከእኛ የተሻለ ሰው ስላልነበረ በእኛ ግምት ጥልቀት አለው ብለን የምናስበውን ትምህርት እንሰጥ ነበር።

የዚያ ወንድም ነቀፋና ትችት ሲበዛብን ምናልባት ይህ ወንድም ይህቺን የማስተማሯን ሥፍራ ፈልጎት ይሆናል ብለን አሰብን። አንድ ቀን “ይህ ወንድማችን እኛ የምንሰጠው ትምህርት ጥልቀት ከሌለው ለምን እርሱ ጥልቀት አለው የሚለውን ትምህርት እንዲያስተምር ዕድል አንሰጠውም” ብለን ተወያየንና ቅዳሜ ከሰዓት በኋላ ባለው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ፕሮግራማችን ላይ እንዲያስተምር ዕድል ሰጠነው። አንድ ሳምንት ያህል በደንብ ከተዘጋጀ በኋላ ሊያስተምር መድረኩ ላይ ወጣ። አንድ ጥቅስ ካነበበ በኋላ “ጥልቀት አለው” የሚለውን ትምህርት

ማስተማሩን ጀመረ። እንኳን “ጥልቀት ያለው” ትምህርት መስጠት ቀርቶ ትክክል የሆነ አረፍተ ነገር እንኳን መሥራት አቃተው። አፉ ተሳሰረ። ጊዜው ሞቃታም ባይሆን በፍርሃት ላብ በላብ ሆነ። ከዘፍጥረት እስከ ራዕይ ድረስ ብዙ ጥቅሶች አነበበ፤ ግን ሀሳቡ ሊገጣጠምለት አልቻለም። “ከበሮ በሰው እጅ ያምር፥ ሲይዙት ግን ያደናግር” እንደሚሉት ሆኖበት ተደናግሎ ከመድረኩ ወረደ። ያ ወንድም ከዚያ ቀን በኋላ ሲያሞግሰን ባንሰማም “የምተሰጡት ትምህርት ጥልቀት የለውም” ብሎ ሲነቅፈን ስምተን አናውቅም። አንዳንድ ሰዎች መድረክ ሲፈልጉ የሚፈልጉትን ማግኘት የሚችሉት ሌሎችን አሳንሰው በመናገር ስለሚመስላቸው በሚያገለግሏቸው ሰዎች ላይ የነቀፋና የአሉባልታ ዘመቻ ያካሂዳሉ። የአገልጋዮቻቸው የአሰባበክ ችሎታ እንከን አይወጣለትም ወይንም በአገልጋዮች የአሰባበክ ችሎት አስተያየት የሚሰጡት ሁሉ መድረክ ፈልገው ይሆናል ማለት አይደለም። ያም ሆነ ይህ ገንቢ ያልሆነ ነቀፋ ነቃፊውንም ሆነ ተነቃፊውን አይጠቅምም። “ወንድሞቼ ሆይ! እርስ በርሳችሁ አትተማሙ፤ ሰውን የሚያማ ወይም በሰው ላይ የሚፈርድ ሕግን ያማል፤ በሕግም ላይ ብትፈርድ ፈራጅ መሆንህ ነው እንጂ ሕግን ፈጻሚ አይደለህም” (ያዕቆብ 4፥1)።

## ለ. በጥላቻ ምክንያት ይነቅፋሉ

ተነቃፊው በእርግጥ የሚያስነቅፈው ነገር ሳይኖረውም ከጥላቻ መንፈስ ብቻ የሚመጣ ነቀፋ አለ። አንዳንድ በሚጠሉት ሰው ላይ ድካም ወይንም ጉድፍ ለማግኘት ሲሉ መብራት አብርተው የሚፈልጉ ሰዎች አሉ። የሕይወቱን አሮጌ ፋይኖች (dead files) ያገላብጣሉ። የሚፈልጉትን በቀላሉ ማግኘት ካልቻሉ በገንዘባቸው ቀጥረው የሚያሰልሉም አሉ። ጂሚ ስዋገርት ድካም ቢኖርበትም በድካሙ እንዲጋለጥ ያደረገው ቀደም ሲል ጂሚ ስዋገርት በተመሳሳይ ኃጢአት ምክንያት ከአገልግሎቱ እንዲባረር ያደረገው ሰው ነው። ያ ሰው ጂሚ ስዋገርትን እንደ ጠላቱ ይመለከተው ስለነበረ እርሱን መልሶ የሚወጋበት መንገድ ይፈልግ ነበር። ለብቻው እንደማይስካለት ስላወቀ የሚገባበትንና የሚወጣበትን ቦታ እንዲከታተሉ ቅጥር ሰላዮችን አዘጋጀ። እንዳሰበውም “ጠላቴ ሆይ አገኘሁህ” አለው። የእግዚአብሔር ቃል ስለእንደዚህ ዓይነት ሰዎች ጥሩ አድርጎ ይናገራል። “ለሌሎች ወጥመድን የሚዘረጉ ሰዎች ራሳቸው ይያዙበታል፤ በሰው ላይ የሚሰዱት የድንጋይ ናዳ እነርሱን መልሶ ይጎዳቸዋል። የምትጠላውን ሰው በሃሰት ልትጎዳው ትችል ይሆናል፤ ነገር ግን ሐሰት የሆነ ልዝብ ንግግር ከጥፋት በቀር የሚያስከትለው ነገር የለም” (ምሳሌ 26፥27-28)።

## ሐ. በቅናት የተነሳ ይነቅፋሉ

ድሮ በአገራችን አንዳንድ ሰዎች ሕጻናትን “ፍቅር እንዴት ያደርጋል?” “ቅናት እንዴት ያደርጋል?” እያሉ ይጠይቁ ነበር። ሕጻናቾችም ከአሳዳጊያቻው እንደ ተነገራቸው እጃቸውን እያነፉሱ (እያራገቡ) “ፍቅር እንዲህ ያደርጋል” እርር ኩምትር እያሉ “ቅናት ደግሞ እንዲህ ያደርጋል” ይሉ ነበር። እርግጥ ነው ቅናት የሞላበት ሰው በውስጡ እርር፣ ኩምትር ይላል። የእግዚአብሔርም ቃል እንዲህ ይላል። “ፍቅር እንደ ሞት የበረታች ናት፤ ቅንዓ ትም እንደ መቃብር የከፋች ናት፤ በምትነድበትም ጊዜ እንደ እሳት ወላፈን ትገርፋለች”(መኃልየ መኀልየ 8፥6)። ስለሆነም ያን የሚቀናበትን ሰው ለማጥፋት ባለው ሃይልና ጥበብ ይጠቀማል። ያንን ሰው ለመጉዳት የማያስወራው ወሬ፣ የማያደርገው ነገር የለም። ነብዩ ዳንኤል በዳርዮስ መንግሥት ውስጥ ከፍተኛ ስልጣን ነበረው። ከሌሎቹ መሳፍንት ሁሉ የሚበልጥ መሆኑን በተግባር ስላስመሰከረ ንጉሡ በመንግሥቱ ሁሉ ላይ ኃላፊ አድርጎ ሾመው። ይሄም አንዳንዶቹን አስቆጣቸው። በቅናትም ተነሳስተው እርሱን የሚጥሉበት መንገድ ይፈልጉ ነበር። ደስ የሚያሰኘው በዳንኤል ላይ ክስ የሚመሰርቱበት ወንጀል አጡበት። “…በዳንኤልና በሚያከናውነው ሥራ ላይ ክስ ለመመሥረት የሚያስችለውን ወንጀል ለማግኘት ፈልጉ፤ ነገር ግን ዳንኤል እጅግ ጠንቃቃና ታማኝ ስለነበር ምንም ዓይነት ስህተት ወይም በደል ሊያገኙበት አልቻሉም” ይላል (ዳንኤል 6፥4)። በቅንአት ተነሳስተው ከሕይወታችን ውስጥ ጉድፍ ለሚለቅሙ አንዳንድ ሰዎች መንገድ ላለመስጠትና ቀዳዳ ላለመክፈት በሕይወታችን ጠንቃቃ ኑሮ መኖር ያስፈልገናል። ጳውሎስም በዚህ ሀሳብ ላይ ይመክረናል። “አገልግሎታችን እንዳይነቀፍ በምንም ነገር ለማንም መሰናከያ አንሆንም” ይላል (2ኛ ቆሮንቶስ 6፥3)።

## መ. ራሳቸውን ለማተለቅ ሲሉ ሌላውን ይነቅፋሉ

ነቀፋቸው ሌላውን ሰው የሚጎዳ መሆኑን ቢያውቁም ስለ ሌሎች ዝቅተኛ አስተያየት በመስጠት ራሳቸውን አተልቀው ለማሳየት የሚሞክሩ አሉ። እንደእነዚህ ዓይነት ሰዎች ሌላውን ማመስገንና ማድነቅ የማይችሉ

ከመሆናቸውም ሌላ ሌሎችም እነዚያን ሰዎች ሲያመሰግኑአቸው መስማት አይፈልጉም። ማድነቅ ስንል ያልሆኑትን እንደሆኑ፣ ያላከሉትን እንዳከሉ አሳድጎና አተልቆ ማውራት ማለታችን አይደለም። የአሰባበክ ሥርዓት ተከትሎ ተጨባጭ የሆነ ነገር ለአድማጮቹ መስጠት የሚችለውንም ሰባኪ "ስብከቱ ፈጽሞ አይረባም" ይላል። ስብከቱን ማጥላላት ፈጽሞ የማይችል መሆኑን ከተረዳ ደግሞ ሌሎች ሰዎች ሊመዝኑት የማይችሉት ድክመት እዳለበት ማውራት ይጀምራል። "መድረክ ላይ ብቻ ቢወዛወዙ ምን ያደርጋል! የሚሰብከው ስብከት ከሚኖረው ሕይወት ጋር አብሮ አይሄድም" ይላል። ይህ ሰው ዋና ዓላማው "እኔ ከእርሱ እበልጣለሁ" ለማለት ብቻ ነው።
ጳውሎስ ራሳቸውን ከፍ አድርገው ስለሚናገሩት አንዳንድ ሰዎች እንዲህ ሲል ይጽፋል። "…ራሳቸውን ከሚያመሰግኑ ከአንዳንድ ሰዎች ጋር ራሳችንን ልናወዳድር ወይም ራሳችንን ልናነጻጽር አንደፍርም፤ እነርሱ ግን ራሳቸውን ከራሳቸው ጋር በማወዳደራቸው አስተዋዮች አይደሉም። እኛ ግን እስከ እናንተም እንኳ እስከንደርስ እግዚአብሔር በሰጠን የሥራ ክልል እንመካለን እንጂ ከመጠን በላይ የምንመካ አይደለንም" (2ኛ ቆሮንቶስ 10፥12 -13)።

**ሠ. ሌላውን መንቀፍ ደስ ስለሚላቸው ብቻ ይነቅፋሉ**

ሁለት ፈጽሞ የማይጣጣሙ ሰዎች በጣም ጥሩ ወዳጆች የሚሆኑበት ጊዜ አለ። ያም ተገናኝተው ሌላውን ሰው ቁጭ ብለው መንቀፍ፣ መተቸትና ማማት ሲችሉ ነው። በዚህ ላይ ፍልጎታቸው አንድ ዓይነት ስለሆነ ከመስማማታቸውም ሌላ አራት ሰዓት ቁጭ ብለው ስለ ሌላው ሰው ቢያወሩ አይሰለቻቸውም። ጥንት የቤተክርስትያን ሽማግሌዎች ሆነን ስናገለግል ሳምንታዊ የሽማግሌዎች ስብሰባ ነበረን። በየሳምንቱ ሰኞ ሲደርስ "ወህኒ ቤት ትገባለህ" የተባልሁትን ያህል እፈራውና እጠላው ነበር። የሚገርመው አሁንም በአሜሪካውያን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሽምግልና አገለግላለሁ። በወር አንድ ጊዜ "ሰኞ" የሽማግሌዎች ስብሰባ አለን። ታዲያ የድሮው ትዝ እያለኝ ዛሬም "ሰኞ" ሲደርስ እንደንግጣለሁ። የጥንቱን የሽማግሌ ስብሰባዎቻችንን የጠላሁት ብዙዎቻችን ገና ልጆች ስለነበርን በስብሰባችን ወቅት ብዙ እንጨቃጨቅ ስለነበር ነው። ሳንጨቃጨቅ፣ ደስ ብሎን፣ የምናደርገው ስብሰባ ከመካከላችን አንደኛችንን ወይንም ከውጪ አንዱን በመንቅፍና ብያኔ በምናስተላልፍበት ጊዜ ነበር። ይሄ በጣም ይገርመኝ ነበር። ይሄም የሰው ባህሪ መሆኑን መማር ቻልኩ። አብዛኛውን ጊዜ የማይስማሙ ሁለት ሰዎች የመንቀፍ ዝንባሌ ካላቸው ሳያውቁት ሲቀራረቡና ሲፈላለጉ ይታያሉ። ስለዚህ ተሰብስበው ነቀፋ የሚያካሂዱ ሰዎች እንደዚያ ያቀራረባቸውን ምክንያት ስለምናውቅ እነርሱ ዓላማችንን ይገለበጡብናል ብለን አንፍራ። "ይጎዳል" ብለው ያሰቡት ሰው ቀጥ ብሎ ሲሄድ ሲያዩ ተስፋ ቆርጠው አንድነታቸው ይቀዘቅዛል። ሰውን በመንቀፍ ልዩ ደስታ ከሚሰማቸው ጋር ጓደኛ እንዳንሆን የእግዚአብሔር ቃል ይመክረናል።

**5ኛ. ለነቃፊዎች እንርበትበት**

ነቀፋ ሲደርስብን ረጋ እንበል። ዓለም በላያችን የተደፋብን መስሎ አይሰማን። በሕይወታችን አንድ በጎ ነገር ለማደርግ ቆርጠን ስንነሳ ነቀፋ እንደሚደርስብን አስቀድመን በማወቅ አቋመ ቢስ፥ የምንይዘውና የምንጨብጠው የሌለን አንሁን። አንድ የሥነ መለኮት ትምህርቱን አጠናቆ የአንድ ቤተ ክርስትያን መጋቢ የሆነ ወጣት ነበር። አገልግሎቱን ከጀመረ ገና አንድ ዓመቱ ነው። አንድ ዕሁድ ስብከቱን ጨርሶ ከመድረኩ ሲወርድ ከቤተ ክርስትያን አባሎች አንዱ ሰላምታ ከሰጠው በኋላ "አንተ በጣም ጥሩ ሰው ነህ፤ የጸሎት ሥርዓትህ ግን ፍጹም ያልበሰለ ነው" አለው። ይሄ አነጋገር ያንን መጋቢ ስብርብሩን አወጣው። የተሰማውን ራሱ ሲገልጽ "ይህን ከሰማሁ በኋላ መብላት፣ መተኛት፣ ማጥናት፣ አባሎቼን መጎብኘት፣ በጠቅላላው ሳምንቱን ሙሉ ምንም ነገር መሥራት አቃተኝ። ሕይወቴ ሁሉ ዝብርቅርቁ ወጣ" አለ። ይህ መጋቢ "ነቀፋ" ሳያንቀው፣ ስሜቱ ከቁጥጥር ውጪ ሳያደርገው ራሱን አረጋግቶ ማለፍ አልቻለም ነበር። ይህንን ዓይነቱ ነገር በአገልግሎት ውስጥ መኖሩን ትምህርት ቤት ሳለ የተማረው አይመስለንም። በአገልግሎቱ ለመዝለቅ ከፈለገ ግን ይህንን በግድ መማር አለበት። "የሰባኪዎች ቁንጮ" እየተባለ ከሚጠራው ስፐርጀን ሥር እንዲሁም በዘመኑ ተደናቂ ከሆነው አሜሪካዊ ሰባኪ ከቻርለስ ስዊንደል እግር ሥር ሆነው ወንጌልን ከሰሙት መካከል እንኳን "በቂ መንፈሳዊ ምግብ አልተመገብንም" በማለት የሚነቅፉ ሰዎች እንደማይጠፉ እንገምታለን። አንዳንድ ሰዎች ነቀፋን ለመቀበል ደካሞች ናቸው። ምን ማድረግ እንዳለባቸው አያውቁም። ጥሩ ነገር ይዞላቸው እንኳን ብቅ ቢል እንዴት እንደሚጠቅሙበት አያውቁም። የሚቀላቸው ቁጭ ብለው ለራሳቸው ማዘንና ማልቀስ ብቻ ነው። ስለዚህ ነቀፋ ሲደርስብን ሳንርበተበት ስሜታችንን በቁጥጥር ሥር አውለን ወደፊት እንራመድ። ማንም ሰው ስሜቱ ተረብሾበት ፍሬ ያለው ሥራ መሥራት አይችልም። ሥራችን በዚህ ምክንያት ወደ ኋላ ቢል ለሚነቅፉን ሰዎች ትልቅ ድል የምናስጨብጣቸው መሆኑን አንዘንጋ።

**6ኛ. ለእግዚአብሔር አሳልፈን እንስጠው**

ነቀፋ ሲደርስብን በጥሩ መንፈስ እየጸለይን እንቀበለው። "ይሄ የደረሰብኝ ነቀፋ እውነት ነው? ትክክል ነው? ከዚህ ውስጥ በሕይወቴ ምን እማርበታለሁ?" በማለት ክርስትያኖች ራሳችንን በትዕግሥት መጠየቅ አለብን። አንዳንድ ጊዜ እኛን ለመስበር የተወረወረ ክፉ ቃል እንኳን ቢሆንም መልካም ነገር ልናገኝበት እንችላለን። ጸሎትና "የተፈጥሮ ችሎታን" (common sense) ከተጠቀምን ነቀፌታ ሲደርስብን አሸናፊዎች እንጂ ተሸናፊዎች አንሆንም። ዳዊት በወቅቱ በምላሳቸው ሊጎዱት በተነሱት ጠላቶቹ ላይ እሮሮውን ወደ እግዚአብሔር አሰማ። "እግዚአብሔር ሆይ! ከክፉ ሰዎች አድነኝ፤ ከጨካኞችም እጅ ጠብቀኝ። እነርሱ ሁልጊዜ ክፉ ነገር ለማድረግ ያሤራሉ፤ ዘወትርን ጥልን ያንሣሣሉ፤ ምላሳቸው እንደ መርዛም እባብ ተናዳፊ ነው፤ ቃላቸውም እንደ እፉኝት መርዝ ነው" አለ (መዝሙር 140፥1-3)።

አሮንና እህቱ ማርያም በወንድማቸው በሙሴ ላይ ነቀፋ ያሰሙ ነበር። ሕዝቡ ሙሴን ያከብረው ስለነበረ ክብሩን ለመሻማት ይመስላል ማይራምና አሮን "እግዚአብሔር የተናገረው በሙሴ አማካይነት ብቻ ነውን?" በእኛስ አማካይነት ተናግሮ የለምን?" አሉ (ዘኁልቁ 12፥2)። ደግነቱ ነቀፋቸውን እግዚአብሔር ራሱ ሰምቶ መልሱን ስለሰጠለት ሙሴ መናገር አላስፈለገውም። "…እኔ ከእርሱ ጋር ቃል ለቃል በግልጥ እነጋገራለሁ እንጂ ስውር በሆነ አነጋገር አልናገረውም፤ እንዲያውም እርሱ እኔን በግልጥ አይቶኛል፤ ታዲያ እናንተ አገልጋዬን ሙሴ በመንቀፍ የሐሜት ቃል ለመናገር እንዴት ደፈራችሁ?" አላቸው (ዘኁልቁ 12፥8)። በእኔና በእናንተም ላይ በመንቀፍ የሐሜት ቃል ለሚያወሩትና ለሚያስወሩት እኛ ሳንሆን እግዚአብሔር መልስ እንዲሰጥበት ለእርሱ እንተውለት። እግዚአብሔር ለሁላችንም ዓላማ አለው። ስለሆነም ምንም ዓይነት ነቀፌታ ቢደርስብንም ለጌታ አሳልፈን በመስጠት ወደፊት እንንቀሳቀስ። ባለን ኃይልና ችሎት እየሠራን እንለፍ።

***ለነቃፊዎች ጠቃሚ ምክር***

***ሀ. ገንቢ እንጂ አፍራሽ አንሁን***

አንድ አዋቂ ሰው "በዓለም ውስጥ ሁለት ዓይነት ሰዎች አሉ፤ አንደኛው "አናጢ" ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ "ነቃፊ" ነው አለ። "አናጢው" የገንቢው ክፍል ሲሆን ይገነባል፣ ያሳድጋል፣ እንዲሁም ያቆነጃል። እንዲህ ዓይነቱ በዓለም ዙሪያ ይፈለጋል፤ ላለበት ሕብረተሰብ ጠቃሚ በመሆኑ እግዚአብሔርም ይባርከዋል። "ነቃፊው" ግን "ሰው በላ" ሲሆን በሰዎች ውድቀትና ስህተት ራሱን የሚያዝናናና የሚያስደስት ነው። "ነቀፊ" በራሱ ድካም የታሠረ ምስኪን ሰው ነው። በሚነቀፈው ነቀፋ የራሱን ድካም አጋልጦ ያሳያል። ይህን ዓይነቱ ሰው ያለው መክሊት አንድ ብቻ ነው። ያም ሌሎችን መንቀፍ ብቻ ነው። ታዲያ ለእንደዚህ ዓይነቱ ሰው የተሻለ የሚሆንለት ወይንም የሚበጀው በወንጌሉ ውስጥ አንድ መክሊት ኖሮት ያችኑ ወስዶ እንደቀበረው ሰው  እርሱም ከሚጠቀምበት ይልቅ ቢቀብረው ነው።

**ለ. ሌላውን በመንቀፍ የራሳችንን ድካም አናውጅ**

ኢየሱስ ስለነቃፊዎቹ ሲናገር "… በአንተ ዐይን ያለውን ግንድ ሳታይ ስለምን በሌላ ሰው ዓይን ያለውን ጉድፍ ትመለከታለህ? ደግሞስ በአንተ ዓይነ ያለውን ግንድ ሳታይ ሌላውን ሰው እስቲ በዓይንህ ያለውን ጉድፍ ላውጣልህ እንዴት ትለዋለህ? አንተ ግብዝ! አስቀድመህ በአንተ ዓይን ያለውን ግንድ አውጣ፤ ከዚያም በኋላ በሌላው ሰው ዓይንት ያለውን ጉድፍ ለማውጣት አጥርተህ ታያለህ" ይላል (ማቴዎስ 7፥3፥5)። ግብዝ በራሱ ላይ ያለውን ግንድ ሳይመለከት በሌላው ላይ ያለውን ጉድፍ ላንሳ ይላል። በራሱ ዓይነት ላይ ያለው ትልቅ ግንድ ሳይሳስበው በሌላው ላይ የሚያየው ትንሽ ጉድፍ ያሳስበዋል። ኢየሱስ ይህንን ሲል በቤተ ክርስትያን ስርቆት፣ በማጭበርበርና መዋሸት ሲሰለጥን ዝም እንበል ወይንም በቤተ ክርስትያን ውስጥ ሥርዓት የሚተላለፉትን መቅጣትና ሥነ ሥርዓት ማስያዝ የለብንም ማለቱ አይደለም። ይህ ቢሆን ኖሮ የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 18 ላይ የተጠቀሰው ሥርዓት ባልተጻፈም ነበር። የዘመኑ የሥነ አዕምሮ ዕውቀት ጠቢባን የሰውን የተፈጥሮ ባህሪ በመስታወት ይመስሉታል። ይኸውም ሰዎች "በሌላው ሰው ላይ አየን" የሚሉት ራሳቸው የደከሙበትን ነው" ይላሉ። አንድ ፈላስፋ "በሌሎች ላይ ስንፈርድ የራሳችንን ድብቅ ስህተት በጥሩምባ ማወጃችን ነው" ያለው እውነት ነው። አዕምሮአችን በነቀፋ የተሞላ ከሆነ ጠባያችንን በግልጥ የሚያሳይ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ያረጋግጥልናል። "ውሃ

እንደ መስታወት ሆኖ ፊትህን እንደሚያሳይህ አዕምሮህም እንደ መስተዋት ሆኖ የራስህን ጠባይ ያሳይሃል” ይላል (ምሳሌ 27፥19)።

**ሐ. እንዳይፈረድብን አንፍረድ**

ኢየሱስ “በእናንተ ላይ እንዳይፈረድባችሁ በማንም ሰው ላይ አትፍረዱ፤ ምክንያቱም በሌሎች ላይ በምትፈርዱበት ዓይነት በእናንተም ላይ ይፈረድባችኋል፤ እንዲሁም በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ይሰፈርባችኋል” ይላል (ማቴዎስ 7፥1-2)። እዚህ ላይ ኢየሱስ የሚለን ሌሎችን መንቀፍና በሌሎች ላይ መፍረድ ልክ አለመሆኑንና የእውነተኛ የክርስትያን ባህሪ አለመሆኑን ነው። ስለሆነም በሌሎች ላይ ስንፈርድ በእኛም ላይ የሚፈረድብን መሆኑን ያስገነዝበናል።

**መ. ምላሳችን ሌላውን እንደሚጎዳ እንወቅ**

ምላሳችን ማንነታችንን ያሳያል፤ ሩህሩሆች ወይንም ጨካኞች መሆናችንን ያመለክታል። የምንመዝነው ባለን ጠባይ ሳይሆን በሰዎች ላይ ክፉም ሆነ ደግ በምንናገረው ነገር ነው። በእኛ መልስ ምክንያት የሌላው ጥሩ ስም ይበላሻል፤ እኛ በምናወራው ወሬ ሌላው ከዕለት ሥራው ይባረራል፤ ትዳሩ ይፈርሳል፣ ወይንም የሰዎች አንድነት ይደፈርሳል። ለዚህ ሁሉ ተጠያቂዎች ነን። በአግባቡ ካልተጠቀምንበት ምላስ አጥፊ ወይንም ገዳይ ሰይፍ ሊሆን ይችላል። የእግዚአብሔርም ቃል ይህን ያረጋግጥልናል።

..............................................................................

**በሚቀጥለው ክፍል እስክንገናኝ፥ የጌታ ጸጋና ሰላም ከሁላችን ጋር ይሁን።**